**Buusaa Gonofaa**
**Microfinance S.C./ *W.A.***
***Maayikroofaayinaansii***

ቡሳ ጎኖፋ
ማይክሮፋይናስ (አ.ማ.)

**ሚያዝያ 28 ቀን 2017 ዓ.ም.**

# የባለአክስዮኖች 19ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ፣

የቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ. የ19ኛዉ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 366(1) መሠረት በማህበሩ የዲሬክተሮች ቦርድ በተደረገ ጥሪ ከዚህ ቀደም ታህሳስ 12 ቀን 2017 ዓ.ም. በኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል መደረጉ ይታወሳል። ነገር ግን ይህ ጉባኤ የተከናወነዉ በንግድ ሕጉ እንደተቀመጠዉ፡ ከተፈረመዉ ጠቅላላ የአክሲዮን ብዛት ውስጥ ቢያንስ 1/4ኛዉን ያህል የሚሆን የካፒታል ክፍያ ተደርጎ ሳይጠናቀቅ በንግድ ሕጉ ከተቀመጠዉ አካሄድ ዉጭ በስህተት የተከናወነ በመሆኑ፤ በብሔራዊ ባንክ በኩል ቃለጉባኤዉ ሳይጸድቅ ዉድቅ ሊደረግ ችሏል። ይህንን የአካሄድ ግድፈት ለማረም እንዲቻል ይህ 19ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እንደገና በድጋሚ ሚያዝያ 28 ቀን 2017 ዓ.ም በዳይሬክተሮች ቦርድ ተጠርቷል። በዚሁ መሰረት የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ግንቦት 23 ቀን 2017 ዓ.ም. ከ**ጧ**ቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ በዲሪምላይነር ሆቴል ይካሄዳል። ስለሆነም የተከበሩ ባለአክሲዮኖች በተጠቀሰው ቀን በጉባኤው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

## 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ፣አ.አ. ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 312፣ ዌብ ሳይት www.bgmfi.com ኢ-ሜይል info@bgmfi.com ፖስታ ሣ. ቁጥር 24850 ኮድ 1000፣ ስልክ ቁጥር +251-114-16-26-21፣

1.2. የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፣-KK/AA/3/0001649/2004፣

1.3. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፣ 75,000,000፣

1.4. የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፣ 75,000,000፣

## 2. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

2.1. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች ማጽደቅ፣

2.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.አ.አ. የ2023/24 ሂሳብ ዓመት የሥራ ክንውን ሪፖርት መስማት እና ተወያይቶ ማፅደቅ፣

2.3. የውጭ ኦዲተሮችን እ.አ.አ. የ2023/24 የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት መስማት እና መርምሮ ማፅደቅ፣

2.4. የ 2023/24 ሂሳብ ዓመት ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ዓመታዊ የሥራ ዋጋ ክፍያና አበል መወሰን፣

2.6. የዉጭ ኦዲተሮችን መሾም እና የሥራ ዋጋ ክፍያቸዉን ተወያይቶ መወሰን፣

2.7. የተከፈለ አክሲዮን መጠን ማሳወቅ ፣

2.8. የሕጋዊ መጠባበቂያ ገንዘብ መጠን መጨመር፣ እና

2.9. የጉባዔዉን ቃለ-ጉባኤ መስማትና ማፅደቅ ናቸዉ።

## 3. ማሳሰቢያ

3.1. በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ሥልጣን ባለው የመንግሥት ተአካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በ**ቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር ዋና መሥሪያ ቤት** በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ በመሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

3.2. የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ፤ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤ ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ብጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን።

**የቡሳ ጎኖፋ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር ዳይሬክተሮች ቦርድ**